712/2013

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

17/2015

# የሴክተር ተቋማት ዕቅድ አፈጻጸም ምዘናና ግብረ-መልስ መመሪያ

## ቁጥር 712/2013

ታህሳስ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግለጫ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተጣለበትን ዘርፉን የመምራትና የማስተባበር ድርሻውን በመወጣት ልማትን ለማፋጠን፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችሉ የተለያዩ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን በመለየት ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ የስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን አፈጻጸም ውጤታማነት እና ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የሴክተር ተቋማትን አፈጻጸም ደረጃ በመለየት እውቅና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በፌደራል፣ በክልሎች እና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የእቅድ አፈጻጸም በየወቅቱ መመዘን ተገቢ ነው፡፡

በመሆኑም የሴክተር ተቋማት ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ትግበራ መሳካት የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዲችሉ የዕቅድ አፈጻጸማቸውን በመመዘንና ብቃታቸውን በመለየት እውቅና ለመስጠት የሚያስችል ወጥነት ያለው መመዘኛ መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

ከዚህ አኳያ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 10 (1) (ሠ) አንቀጽ 25 እና ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ሁኔታዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ «የሴክተር ተቋማት ዕቅድ አፈጻጸም ምዘናና ግብረ-መልስ መመሪያ ቁጥር 712/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ሚኒስቴር"** ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነው፣
2) **"ክልል"** ማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣
3) **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት በህግ ወይም በሚመለከተው መንግስታዊ አካል ውክልና የከተማ አስተዳደር ስልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፣
4) **"አብይ ኮሚቴ"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን አካላት ያሰውና ለሚቋቋመው የምዘና የቴክኒክ ኮሚቴ አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን በመስጠት የሚደግፍና የሚያመቻች አካል ነው፣
5) **"የምዘና ቡድን"** ማለት ምዘናውን በአካል በየክልሎቹና ከተማ አስተዳደሮቹ በመገኘት የሚያከናውኑ ሲሆን ስለ ሥራውም በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን የያዘ ቡድን ነው፣
6) **"ስትራቴጂያዊ አመራር"** ማለት የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች እና በሚኒስትሩ የሚወከል አንድ ግንባር ቀደም አመራር ያካተተ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ደረጃ የሚቋቋም ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፣
7) **"ሴክተር ተቋማት"** ማለት በፌዴራል፣ በክልሎች፣ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ማለት ነው፣
8) **"የሴክተር ጉባኤ"** ማለት በፌዴራል፣ በክልሎች፣ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት መካከል በየዓመቱ ሁለት ጊዜ የሚካሄድ ስብሰባ ነው።

9) **"የፌዴራል ተቋማት"** ማለት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥር ተደራጅተው እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ተቋማት ማለት ነው፣

10) **"ምዘና"** ማለት የዘርፉ ሴክተር ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ግንባታ እና የልማት ሥራዎች ከዕቅድ ክንውን አኳያ መመዘን ማለት ነው፣

11) "ደረጃ" ማለት በዚህ የምዘና መመሪያ መሰረት በምዘናው የሚካተቱ የፌዴራል ተቋማትና ክልሎችን የእቅድ አፈጻጸም የሚያሳይ ደረጃ ማለት ነው፣

12) **"ግብረ-መልስ"** ማለት የሴክተር ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ተካሂዶ የምዘና ቡድኑ በሚያቀርበው ውጤት እና መጨረሻ ላይ ውሳኔ በሚሰጠው አካል በጸደቀው የተጠቃለለ ውጤት መሠረት ለተቋማቱ የሚሰጥ ማበረታቻ ወይም የማሻሻያ ድጋፍ ማለት ነው።

## ክፍል ሁለት

## የሴክተር ተቋማት ምዘና

### 3. የምዘናው አስፈላጊነት

የሴክተር ተቋማት የእቅድ አፈጻጸም ምዘና ማካሄድ በሚከተሉት ጉዳዮች ምክንያት አስፈላጊነቱን ያመላክታል።

1) በፌዴራል፣ በክልሎች፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከማሳካት አኳያ የአፈጻጸም ደረጃውን ለመረዳት የሚያስችል በመሆኑ፣
2) በሴክተር ተቋማቱ መካከል ጤናማ የውድድር ስሜት በመፍጠር ለተሻለ አፈጻጸም የሚያነሳሳ በመሆኑ፣ እና
3) በሴክተር ተቋማቱ የተሻሉ መልካም ተሞክሮዎችን በመለየት ወደ ሌሎች ተቋማት ለማስፋት የሚያስችል በመሆኑ አስፈላጊነቱን ያጎላዋል።

### 4. የምዘናው ዓላማ

ይህ በፌዴራል፣ በክልሎች፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት መካከል በተደረሰበት የጋራ መግባቢያ ሰነድ

መሰረት ለበጀት ዓመቱ የተያዘው ዕቅድ በወቅቱ እየተከናወነ መሆኑን ለመመዘን የወጣ መመሪያ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

1) በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በፌዴራል፣ በክልሎችና በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ተጣጥሞ መተግበሩን ለማረጋገጥ እና ያለበትን ደረጃ ለመገንዘብ፣
2) በየተቋማቱ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የለውጥ ሥራ አመራር ሥራዎች አፈጻጸም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እና ከሚጠበቀው ውጤት ጋር ያለውን ክፍተት ለይቶ በማወቅ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ፣
3) የተሻሉ መልካም ተሞክሮዎችን በመለየት ወደ ሌሎች ተቋማት ለማስፋት፣
4) በከተሞች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ፣
5) የከተሞችን ሃብት በተገቢው ሁኔታ በመጠቀም ወደ ልማት ማንቀሳቀስ መቻሉን ለማረጋገጥ፣
6) የተሻለ አፈጻጸም ያሳዩትን ማበረታታትና እንቅስቃሴያቸው አጥጋቢ ባልሆኑ ተቋማት ችግሮቹን በመለየት የሚያደርግላቸውን ድጋፍ ለማጠናከር ናቸው።

## 5. የአፈጻጸም ምዘናው የሚከናወንበት ጊዜ

ምዘናው በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከናወን ሲሆን የመጀመሪያው ዙር በጥር ወር ሁለተኛ ሳምንት እንዲሁም የሁለተኛው ዙር ደግሞ በሐምሌ ወር ሁለተኛ ሳምንት ይካሄዳል።

## 6. የምዘናው መርህ

1) የዘርፉን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ግቦች በላቀ ደረጃ ማስፈጸም፣
2) ጤናማ የሆነ የውድድር ስሜት በሴክተር ተቋማት መካከል መፍጠር፣
3) ለአንድ ዓላማና ለጋራ ውጤት/ስኬት መስራትን ማጎልበት፣
4) በተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ማዳበር፣
5) በተቋማትና በክልሎች መካከል ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋፋት።

## ክፍል ሦስት

## ምዘናውን የሚያካሂዱ አካላት

### 7. ምዘናውን የሚያካሂዱ አካላትን ስለማቋቋም

1) ምዘናው በፌዴራል ደረጃ በተማከለ ሁኔታ የሚከናወን ሲሆን አብይ ኮሚቴ እና ሌሎች የምዘና ቡድኖች ይሳተፋሉ፡፡
2) የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ የምዘና ሂደቱን በዋናነት የሚያስተባብር ይሆናል፡፡
3) ምዘናውን ለማከናወን ከፌዴራል፣ ከክልል እና ከአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተውጣጡ አባላትን የያዘ 14 የምዘና ቡድኖች ይዋቀራሉ፡፡
4) የምዘና ቡድኑ እያንዳንዱ ከአምስት ያልበለጡ አባላት የሚኖሩት እና የተለያየ የሙያ ስብጥር ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ ይሆናል፡፡
5) ለምዘና ቡድን አባል የሚሆኑ ከሥራው ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሙያዎች ያላቸውን ባለሙያዎች እንዲሁም ሥራውን በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ሊያከናውኑ ይችላሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን ባለሙያዎች ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በጥንቃቄ መልምለው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ይልካሉ፡፡

### 8. የአብይ ኮሚቴው አባላት ዝርዝር

1) የከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ.......................................... ሰብሳቢ
2) የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ኃላፊ ............................................... ጸሐፊ
3) የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ........................... አባል
4) የሚኒስቴሩ ጽ/ቤትና የሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ................................ አባል
5) የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ............................................ አባል
6) የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ.................................. አባል ይሆናሉ፡፡

9. የአብይ ኮሚቴው ተግባር እና ኃላፊነት

1) የምዘና ሂደቱን በበላይነት ይመራል፣

2) በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ የሚቀርብለትን የመመዘኛ መስፈርት (check list) ያጸድቃል፣

3) ለምዘናው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን እንዲሟሉ ያደርጋል፣

4) ለምዘናው ሂደት መቀላጠፍ አስፈላጊ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፣

5) የሴክተር ተቋማትን ውጤት መርምሮ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጂያዊ አመራር አቅርቦ ያጸድቃል፣

6) ለሴክተር ተቋማት እንደአፈጻጸማቸው የሚሰጡ ግብረ-መልሶችን የውሳኔ ሃሳብ ለስትራቴጂያዊ አመራር አቅርቦ ያጸድቃል።

10. የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ተግባር እና ኃላፊነት

1) የመመዘኛ መስፈርት (check list) በማዘጋጀት በመመዘኛ መስፈርቱ ላይ የተካተቱ ግቦችና ተግባራት የተሰጣቸው ክብደት (Weight) ከግቦችና ተግባራት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ለየተቋማቱ በማቅረብ ያረጋግጣል፣ ለአብይ ኮሚቴ አቅርቦም ያጸድቃል፣

2) የምዘና ቡድኑ የምልመላ መስፈርት ያዘጋጃል፣ መስፈርቱን ለአብይ ኮሚቴ አቅርቦ ያጸድቃል፣ ሲፈቀድም የምዘና ቡድኑን ይመለምላል፣

3) ለምዘና ቡድኑ የእርስ በርስ ትውውቅ ፕሮግራም በማዘጋጀት ስለምዘናው ሂደት ስልጠና ይሰጣል፣ ቡድኖቹን ወደሚመደቡበት ተቋም ያሠማራል፣

4) ምዘናው የደረሰበትን ደረጃ ይከታተላል፤ ለምዘና ቡድኑ ድጋፍ ያደርጋል፣

5) በምዘናው ወቅት በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ውሳኔም ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣

6) የሴክተር ተቋማቱን የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ከምዘና ቡድኖቹ በመሰብሰብ እና በማጠናቀር በተቋማቱ መካከል የተገኘውን የአፈጻጸም ምዘና ውጤት እና ደረጃ ለአብይ ኮሚቴ ያቀርባል፣ እና

7) የሴክተር ተቋማት ምዘና ውጤት እና ግብረ-መልስ በሚዘጋጅ የሴክተር ጉባኤ መድረክ ላይ ይፋ ያደርጋል።

## 11. የምዘና ቡድን አወቃቀር

1) የምዘና ቡድኑ ከፌዴራል፣ ከክልሎች፣ ከአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ከሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የሚውጣጡ ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን የያዘ ሲሆን በ14 ቡድን ተከፍለው የሚመደቡ ይሆናል።

2) የምዘናው ቡድን ከፌዴራል፣ ከክልሎች እና ከከተማ አስተዳደሮች የተሰባሰቡ ባለሙዎች የተለያየ የሙያ ስብጥር እንዲኖራቸው ተደርጎ ይዋቀራል።

3) የምዘናው ቡድን ከፌዴራል በተውጣጡ ባለሙያዎች የሚመራ ይሆናል።

## 12. የምዘና ቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት እና አስገዳጅ ሁኔታዎች

1) **የምዘና ቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) የምዘና ቡድኑን በተመለከተ የሚሠጡ መግለጫዎችንና ሥልጠናዎችን ይከታተላል፣

ለ) የሥራ እቅድና በዚህ መመሪያ በአባሪነት የተያያዘውን መነሻ በማድረግ የቡድን የሥነ-ምግባር (Code of Ethics) መመሪያ ያዘጋጃል፣ ሥራውን በእቅድ ያከናውናል፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይረከባል፣ ምዘና በሚካሄድበት ተቋም በመገኘት የምዘና ሂደቱን አስመልክቶ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ምዘናውን ያከናውናል፣

ሐ) የምዘና ቡድኑ በየዕለቱ በተመደበበት ቦታ በሰዓቱ በመገኘት ምዘናውን በማካሄድ እና በመፈራረም መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣

መ) ከቸልተኝነት ነጻ በሆነና በመልካም ሥነ-ምግባር ምዘናውን በጥራት ያከናውናል፣

ሠ) በመመሪያው ላይ የተቀመጠውን የአሰራር ስልት በአግባቡ ይተገብራል፣

ረ) ከፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ የሚሰጠውን ተግባር ያከናውናል።

2) **አስገዳጅ ሁኔታዎች**

ሀ) የምዘና ቡድኑ የስነ-ምግባር ደንብ ማዘጋጀት ይኖርበታል፣

ለ) የተካሄደውን ምዘና በየዕለቱ ሞልቶ ሳይፈራረሙ ማሳደር አይቻልም፣

ሐ) የምዘናው ማጠቃለያ የቃል ግብረ-መልስ ለየተቋማቱ መስጠት ይጠበቅበታል፣

መ) የምዘናው የተጠቃለለ ሪፖርት ከስር ከስሩ ተሰርቶ በማጠናቀቅ ቡድኑ ተፈራርሞበት ለፖሊሲና ፕሮግራመ ቢሮ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ማስረከብ አለበት፤ ያልተጠናቀቀ ሪፖርት ተቀባይነት አይኖረውም።

## ክፍል አራት

## የምዘናው አካሄድ እና ነጥብ አሰጣጥ

13. የምዘናው አካሄድ እና አገላለጽ

1) የምዘናው አካሄድ

ሀ) የምዘና ቡድኖች በየተመደቡበት ተቋም በመገኘት ምዘናውን በማካሄድ በየዕለቱ ውጤታቸውን ይሞላሉ፣

ለ) የምዘና ቡድኖች አባላት ውጤት አማካይ የሴክተር ተቋማቱ ውጤት ተደርጎ ይወሰዳል፣

ሐ) የምዘና ቡድኖች በተመደቡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ምዘና ሲያጠናቅቁ ውጤቱን በማጠቃለል ከዝርዝር መረጃዎች ጋር በወቅቱ ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ሪፖርት ያቀርባሉ፣

መ) የምዘና ቡድኖች አጠቃላይ ሪፖርት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዚሁ ተግባር ለተቋቋመው አብይ ኮሚቴ ቀርቦ ከተመረመረ በኃላ ይጸድቃል፣

2) የምዘናው ውጤት አገላለጽ

ሀ) የምዘና ቡድኑ የኢንስፔክሽኑን ውጤት በተለይ የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃና የታየው ጥንካሬና ድክመት ለሚመለከታቸው አካላት ሥራውን አጠናቆ ሲወጣ በተደራጀ መልኩ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

ለ) ባለሙያዎቹ የምዘና ሪፖርቱን አዘጋጅተው በማጠናቀቅ ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ያቀርባሉ፣

ሐ) ፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ሪፖርቱን ለአብይ ኮሚቴው አቅርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

መ) የአብይ ኮሚቴው አስተያየት በሪፖርት ተካቶ ከዳበረ በኂላ ለክልሎች በኢሜል ተልኮ አስተያየታቸውን በ3 ቀናት ውስጥ እንዲሰጡ ይደረጋል፣

4) የተቋማቱን ተገልጋይ/ተጠቃሚ ማነጋገር፣

5) ተቋሙ እቅዱን ለመፈጸም ያደረገው ጥረትና የተጠቀመበት አማራጭ የአሰራር ስልት፣

6) በየዕለቱ ነጥብ በመስጠትና በመፈራረም የየተቋማቱን ሪፖርት ማጠናቀር፣

7) ለየተቋማቱ የማጠቃለያ አስተያየቶችን መስጠት፣

8) በየተቋማቱ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ጨምቆ ማውጣትና የውጤቶቹን ለቡድን መሪው መስጠት፣ እና

9) የተሻለ አፈጻጸም የታየባቸውን ተቋማት በመለየት የተሻሉበትን ሥራና የተሻለ የተከናወነበትን ምክንያት ለይቶ ምርጥ ተሞክሮ መቀመር ይሆናል።

## 16. የምዘናው ነጥብ አሰጣጥ

1) ምዘናው ከላይ በአንቀጽ 15 በተጠቀሱት የምዘና ስልቶችና ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት በተያያዘው የምዘና ቼክሊስት መሠረት ይፈጸማል፣

2) ምዘናው በተመረጡ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቦችና ተግባራት ላይ ያተኩራል፤

3) የዘርፉ የልማት ሥራዎች ካላቸው ትኩረት አኳያ እያንዳንዳቸው ክብደት የሚኖራቸው ይሆናል፣ በዚሁ መሠረት፡-

   ሀ) የለውጥና የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራዎች ................................ 25%

   ለ) የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች ................................................... 23%

   ሐ) የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች ........................................ 14%

   መ) የመልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች ................................ 12%

   ሠ) የመኖሪያ ቤቶች ልማት ሥራዎች................................................ 10%

   ረ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ሥራዎች.......................................... 8%

   ሠ) የከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ሥራዎች.......................................... 8%

   ክብደት የሚኖራቸው ይሆናል።

4) በዚህ አንቀጽ ሥር በንኡስ አንቀጽ 3 (ሀ) የተገለጸው 25% የለውጥና የማስፈጸም አቅም ግንባታ(15%)፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት(5%) እና የዕቅድ ዝግጅት አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ(5%) ሥራዎችን የሚያካትት ይሆናል።

## 17. በክልል፣ በአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የምዘና ሂደት ነጥብ አሰጣጥ፡-

1) የምዘና ቡድኑ የሰጠው የሴክተር ተቋሙ የዕቅድ አፈጻጸም ድምር ውጤት ወደ 90% ይቀየራል፣

2) ቀሪው 10% በፌዴራል ደረጃ የሚገኘው ተመሳሳይ (አቻ) ተቋም የሚሰጠው ውጤት ከ10% የሚሞላ ሲሆን ውጤቱ በተቋሙ ሥራ አመራር ኮሚቴ ጸድቆ ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ በወቅቱ ይተላለፋል፡፡

3) በዚህ በአንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው 10% በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት በፌዴራል ደረጃ የሚገኘው ተመሳሳይ (አቻ) ተቋም ውጤት ይሰጣል፣ መመዘኛ መስፈርቶቹን፡-

| ተ.ቁ | የመመዘኛ መስፈርት | የሥራው ክብደት |
|---|---|---|
| 1 | የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ | 6 |
| ሀ. | ሠነድ ተልኮ አስተያየት ሠጥቶ በወቅቱ መመለሱ | 2 |
| ለ. | ዕቅድና ሪፖርት (ዕቅድ ሲከለስም ለፌደራል ተቋሙ በወቅቱ ስለመላኩ) በወቅቱ መቅረቡ | 2 |
| ሐ. | በስልክና በደብዳቤ ልውውጥ በወቅቱ ምላሽ መስጠቱ) | 2 |
| 2 | የተለያዩ ስብሰባዎችና ወርክሾፖች ላይ መገኘትን በተመለከተ | 2 |
| 3 | ከፌዴራል ቢሮው ለሥራ ከሚሄዱ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የጋራ ፕሮግራምን አክብሮ መገኘትን በተመለከተ | 2 |
| | ድምር | 10 |

4) በክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ተቋማት የምዘና ውጤት በአንቀጽ 17 መሰረት ከ100 ከተሰላ በኃላ በአንቀጽ 16 በንዑስ አንቀጽ (3) በተሰጠው የሥራዎቹ ክብደት መሰረት ተባዝቶ አጠቃላይ የክልሉ ወይም የከተማ አስተዳደሩ ውጤት ይሆናል፡፡

## 18. የፌዴራል ተቋማት ነጥብ አሰጣጥ

የሴክተር ተቋማት ዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ከሚካሄድባቸው አካላት መካከል የሚኒስቴር መ/ቤቱ አንዱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥር የሚገኙ ተቋማት እራሳቸውን ችለው የዕቅድ አፈጻጸማቸው እየተመዘነ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡ እነዚህ ተቋማት በዘርፉ የተለዩ አበይት ተግባራትን ለማስፈጸም የተቋቋሙ በመሆኑ ለምዘና ያመች ዘንድ እነዚህ ሥራዎች መሠረት በማድረግ ለየተቋማቱ ክብደት መስጠት ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ለአበይት

ሥራዎች 60 በመቶ ክብደት እንዲኖራቸው እና የለውጥና የአመራር ሥራዎች 40 ከመቶ ክብደት እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት፦

1) **የከተማ ልማት ዘርፍ ተቋማት (35 በመቶ)**

   ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ..........12

   ለ) የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ተቋማት..........10

   በዚህ ስር የሚካተቱት የከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ቢሮ፣ የተቀናጀ የመሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና የከተማ መሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ኤጀንሲ ናቸው፡፡

   ሐ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ.......... 7

   መ) የከተማ ፕላን ጽዳትና ውበት ቢሮ .......... 6

2) **የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተቋማት (25 በመቶ)**

   ሠ) የመኖሪያ ቤቶችና ልማትና የመንግስት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ..........15

   ረ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪና ሬጉላቶሪ ቢሮ.......... 10

3) **የለውጥ እና የአመራር ሥራዎች ክብደት (40 በመቶ)**

   ሰ) የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ..........15

   ሸ) ፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ.......... 8

   ቀ) ሚኒስትሩ ጽ/ቤት እና የሚኒ-ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ.......... 5

   በ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳታቤዝ ልማት ቢሮ.......... 5

   ተ) የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት.......... 4

   ቸ) የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ.......... 3

   እንዲነፐራቸው ተደርጓል፡፡

## 19. የፌዴራል ምድብ አንድ ተቋማት ነጥብ አሰጣጥ

1) የተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ውጤት ከ100% ከተሞላ በኋላ ወደ 30% ይቀየራል፣
2) የተቋማቱ የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራዎች የምዘና ውጤት በማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ ተመዝኖ ከ15% ይሞላል፣
3) የቢሮዎች የስድስት ወር የGTP መድረክ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ተወስዶ ወደ 20% ከተሰወጠ በኋላ በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ይሞላል፣
4) እንዲሁም 25% የክልል አቻ ተቋማት አማካይ ውጤት ተወስዶ የሚደመር ይሆናል፣

5) የክልል አቻ ተመጋጋቢ ተቋማት ለፌዴራል የሚመለከተው ተቋም ከማስፈጸም አቅም ግንባታ እና ከነበራቸው የሥራ ግንኙነት ረገድ የነበረውን ሚና መዝነው 10 ከመቶ ውጤት ይሰጣሉ፣

6) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (5) የተገለጸው 10% በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት በክልል ደረጃ የሚገኘው አቻ ተመጋጋቢ ተቋም ለፌዴራል የሚመለከተው ተቋም ውጤት የሚሞላ ሲሆን ውጤቱ በተቋሙ ኃላፊ ወይም ተወካይ ተሞልቶና በፖስታ ተሽጎ ለምዘና ቡድኑ ይሰጣል፤ የምዘና ቡድኑም ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ከአጠቃላይ የምዘና ሪፖርት ጋር ያስረክባል። በዚሁ መሠረት የመመዘኛ መስፈርቶቹም የሚከተሉት ናቸው።

| ተ.ቁ | የመመዘኛ መስፈርት | የሥራው ክብደት |
|---|---|---|
| 1 | በፌዴራል ተቋማቱ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ተቋማት የተደረገ የማስፈጸም አቅም ግንባታና ድጋፍን በተመለከተ፡- | 4 |
| ሀ | ፌዴራል ተቋሙ የድጋፍ ዕቅድ አውጥቶ፣ የክልል ተቋሙ እንዲያውቀው በማድረግ የተደረገ ድጋፍ ስለመኖሩ | 1 |
| ለ. | የክልል ተቋሙን የማስፈጸም አቅም ለመገንባት (ስልጠና በማመቻቸት/በመስጠት፣ ግብአት በማሟላት...ወዘተ) የተከናወኑ ተግባራት ስለመኖራቸው | 1 |
| ሐ. | በፌዴራል ደረጃ የተዘጋጁ የህግ ማዕቀፎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ስለመሰራቱ | 2 |
| 2 | በክልል ተቋሙ የቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ፌደራል ተቋሙ በወቅቱ ምላሽ ስለመስጠቱ | 2 |
| 3 | ፌዴራል ተቋሙ ከክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ተቋሙ ጋራ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ በጋራ ገምግሞ ስምምነት ላይ የተደረሰ ስለመሆኑ | 4 |
| | ድምር | 10 |

7) የምድብ አንድ ተቋማት ውጤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) - (6) የተሞላው ተደምሮ አጠቃላይ የተቋሙ ውጤት ከ100% ይሆናል።

## 20. የፌዴራል ምድብ ሁለት ተቋማት ነጥብ አሰጣጥ

1) የተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ውጤት ከ100% ከተሞላ በኋላ ወደ 40% ይቀየራል፣
2) የተቋማቱ የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራዎች የምዘና ውጤት በማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ ተመዝኖ ከ40% ይሞላል፣
3) የቢሮዎች የ6 ወር የGTP መድረክ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ተወስዶ ወደ 20% ከተለወጠ በኋላ በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ የሚሞላ ይሆናል።

## 21. የሴክተር ሥራዎች ነጥብ አሰጣጥ

1) የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ሥራዎች በፌዴራል፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በጋራ የሚፈጸሙ በመሆናቸው የእያንዳንዱ የዘርፉ ሥራዎች የሁሉንም ባለድርሻ አካላትን ውጤት ሊያንጸባርቅ ይገባል፡፡
2) ስለሆነም የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመጨረሻ ውጤት ወደ 90 በመቶ እንዲሁም የፌዴራል ተቋማት ለየክልሉ ለየዘርፉ ከ10 ውጤት እንዲሰጡ በማድረግ ድምር ውጤቱ ከመቶ የሴክተሩ ውጤት ይሆናል፡፡
3) የሴክተር አበይት ሥራዎች፡-
   ሀ) የለውጥና የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራዎች
   ለ) የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች
   ሐ) የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች
   መ) የመልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች
   ሠ) የመኖሪያ ቤቶች ልማት ሥራዎች
   ረ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ሥራዎች እና
   ሠ) የከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ሥራዎች ናቸው፡፡

## 22. የሴክተር ተቋማት ምድብ

የዕቅድ አፈጻጸም ምዘናው በክልሎች እና በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሁለት ምድብ ተከፍለው በክልል ደረጃ የሚወዳደሩ ሲሆን የፌዴራል ተቋማትም በሁለት ምድብ ተከፍለው በፌዴራል ተቋማት መካከል ባስገኙት አፈጻጸም መሰረት በመወዳደር የምዘና ውጤትና ደረጃ የሚወጣ ይሆናል፡፡ ምድቦቹም፡-

1) **የክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የምዘና ምድብ አንድ**
   ሀ) በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
   ለ) በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
   ሐ) በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
   መ) በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
   ሠ) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና
   ረ) በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር

2) **የክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የምዘና ምድብ ሁለት**

ሀ) በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ለ) በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ሐ) በሶማሊ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መ) በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና

ሠ) በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የከተማ ልማትና

ረ) ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት አንድ ላይ የሚወዳደሩ ይሆናል።

3) **የፌዴራል ተቋማት የምዘና ምድብ አንድ**

ሀ) የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ

ለ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ሐ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ

መ) የተቀናጀ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት

ሠ) የከተማ መሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ኤጀንሲ

ረ) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ

ሰ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ሸ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ እና

ቀ) የከተማ ፕላን፣ ፅዳትና ውበት ቢሮ

ተ) የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ

ቸ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ ናቸው።

4) **የፌዴራል ተቋማት የምዘና ምድብ ሁለት**

ሀ) የሚኒስቴሩ ጽ/ቤትና የሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ

ለ) የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ

ሐ) የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት ናቸው።